የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 7
ADDIS ABABA 9th Junuary, 2020


## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፬/፪ሺ፲፪ ዓ.ም


የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራ /ማሻሻያ/ አዋጅ…..ገጽ ፲፪ሺ፸፰

ማረሚያ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፲፪…………………ገጽ፲፪ሺ፹፭


## Content

Proclamation No. 1164/2019


Microfinance Business (Amendment) Proclamation Page …………………………..…………………12078
Corrigendum No.15/2020………………….page 12085


### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፬/፪ሺ፲፪

### የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፮/፪ሺ፩ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል:-

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፬/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፮/፪ሺ፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ (፬) እና (፮)፣ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ (፬) እና (፮) ተተክተዋል፡፡

፫/ "ኩባንያ" ማለት በንግድ ሕግ የተሰጠውን ትርጉም የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ:-

ሀ) በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም በኢትዮጵያውያን እና የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጋራ የተያዘ፣ ወይም

### Proclamation No. 1164/2019

### <u>A PROCLAMATION TO AMMEND MICROFINANCE BUSINESS PROCLAMATION</u>

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Microfinance Business Proclamation No. 626/2009;

**NOW, THEEFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

"This Proclamation may by cited as Microfinance Business (Amendment) ProclamationNo.1164/ 2019."

**2. <u>Amendment</u>**

The Microfinance Business Proclamation No.626/2009 is hereby amended as follows:

1/ Sub Article (3), (4) and (6) of Article 2 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (3), (4) and (6):

3/ "company" means a share company as defined under the Commercial Code, the capital of which is:

a) owned fully by Ethiopian nationals or foreign nationals of Ethiopian origin or jointly owned by Ethiopian nationals and foreign nationals of Ethiopian origin, or

ለ) ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም በኢትዮጵያውያን እና የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጋራ ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ፤

በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ አክሲዮን ማኅበር ነው፣

፬/ "የግዴታ ቁጠባ" ማለት ገንዘቡን የሚቆጥቡት ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ወይም የንግድ ድርጅቶች ፈቃድ ከተሰጠው ተቋም ብድር ለመውሰድ ብቁ ለመሆንና ለሚያገኙት ብድር በመያዣነት እንዲያገለግል በግዴታ የሚያስቀምጡት የቁጠባ ገንዘብ ነው፤

፮/ "የፋይናንስ ተቋም" ማለት መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት፣ በዲጅታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ነው፣

፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፯) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፲፰)፣ (፲፱) እና (፳) ተጨምረው ንዑስ አንቀጽ (፲፰) ንዑስ አንቀጽ (፳፩) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

፲፰/ "በዲጅታል ዘዴዎች የሚሰጥ የፋይናንስ አገልግሎት" ማለት በዲጅታል ዘዴዎች የሚሰጡ የክፍያ፣ የሐዋላ እና የመድን አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡"

፲፱/ "የውጭ ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ" ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ ላይ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡"

፳/ "ገንዘብ አከል ንብረት" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፣

ሀ) ጥሬ ገንዘብ፣

ለ) በሀገር ውስጥ ባንኮች እና በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ያለ ተቀማጭ ገንዘብ፣

ሐ) በቀላሉ ወደ ጥሬ ገንዘብ ተቀይረው ወዲያውኑ ተከፋይ ሊሆኑ የሚችሉ ንብረቶች፤ እና

b) organizations owned fully by Ethiopian nationals or foreign nationals of Ethiopian origin or jointly owned by Ethiopian nationals and foreign nationals of Ethiopian origin;

registered under the laws of, and having its head office, in Ethiopia;

4/ "compulsory savings" means mandatory deposits made for the purpose of enabling the individuals, groups or businesses making the savings to qualify to receive loans from an authorized institution and to serve as collateral against the loans so obtained;

6/ "financial institution" means insurance company, bank, capital goods finance company, micro-financing institution, a reinsurer, a micro insurance provider, postal savings, money transfer institution, an institution providing financial service through digital channels or such other similar institution as determined by the National Bank;

2/ The following new Sub-Articles (18), (19) and (20) are added after Sub Article (17) of Article 2 of the Proclamation, and the existing Sub-Articles(18) is renumbered as Sub-Article (21);

18/ "digital financial service" means financial services including payments, remittances and insurance accessed and delivered through digital channels.

19/ "Foreign National of Ethiopian Origin" means a foreign national of Ethiopian origin as defined under Proclamation No. 270/2002 providing Foreign Nationals of Ethiopian origin with certain rights to be exercised in their country of origin.

20/ "Liquid assets" shall include:

a) cash;

b) deposits with local banks and micro finance institutions;

c) other assets readily convertible into cash; and

መ) በብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ተቀባይነት አላቸው ተብለው የሚወሰኑ ሌሎች ገንዘብ አከል ንብረቶች፡፡"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሰ)፣ (ቀ) እና (ተ) ተሰርዘው በሚከተሉት ፊደል ተራ (ሰ)፣ (ቀ) እና (ተ) ተተክተዋል:-

ሰ) "በከተማና በገጠር በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች ወይንም በሌሎች ምርታማ ተግባራት ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚያካሂዷቸውን ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶች ማገዝ፤"

ቀ)"ለጥቃቅንና ለአነስተኛ የንግድ ሥራዎች ወይም መሰል ምርታማ ተግባራት ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስተዳደር፤"

ተ) "የፋይናንስ ኪራይ አገልግሎት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፩፻፫/፲፱፻፺ እና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፯/፪ሺ፭ መሠረት ለተከራዮች መስጠት፤

፬/ ከአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ተ) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ቸ)፣ (ኀ) እና (ነ) ተጨምረው ነባሩ ፊደል ተራ (ቸ) ፊደል ተራ (ኘ) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

ቸ) "በዲጅታል ዘዴዎች የዲጅታል ፋይናንስ አገልግሎት፣

ኀ) የወኪል ባንኪንግ አገልግሎት መስጠት፤ እና

ነ) ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አገልግሎት መስጠት፣"

፭/ ከአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ቀጥሎ አዲስ ፊደል ተራ (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) ተጨምረዋል፡፡

ሐ) "ተቋሙ የገንዘብ አከል ንብረት እጥረት ሲያጋጥመው፣

መ) ተቋሙ ዕዳ መክፈል ወደማይችልበት ወሰን ሲደርስ፣ ወይም

ሠ) ተቋሙ ህግንና መመሪያን ተቀብሎ ለመስራት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር፤"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡፡

d) Such other assets as the National Bank may from time to time declare to be liquid assets.

3/ Paragraph (g), (i) and (k) of Sub Article (2) of Article 3 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new paragraph (g), (i) and (k):

g) "Supporting income generating projects of urban and rural micro and small scale operators or others engaged in productive activities;"

i) "Managing funds for micro and small scale businesses or other related productive activities;"

k) "Providing financial leasing service to lessees in accordance with Capital Goods Leasing Business Proclamation No .103/1998 and Capital Goods Leasing Business (Amendment) Proclamation No. 807/2013;"

4/ The following new paragraphs (l), (m) and (n) are added after paragraph (k) of Sub-Article 2 of Article 3 of the Proclamation, and the existing paragraph (l) is renumbered as paragraph (o):

l) Provide digital finance services;

m) Agent banking service; and

n) Provide interest-free microfinance service;

5/ The following new paragraph (c), (d) and (e) are added after paragraph (b) Sub Article (1) of Article 8 of the Proclamation:

c) "The institution has become illiquid;

d) The institution has become insolvent ; or

e) The institution has failed to obey and operate in line with the law and directive or is unwilling to do so;"

6/ Sub Article (1) of Article 13 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

፩/ "የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር የኦዲት ግኝቶችን፣ ድምዳሜዎችን እና አስተያየቶችን ያካተተ የተሟላ የኦዲት ሪፖርት እና የውጭ ኦዲተር ዝርዝር ግኝቶችን በብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡ በተጨማሪም የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር የተቋሙን ሂሳብ መርምሮ ያገኛቸውን ውጤቶች እና የደረሰባቸውን ድምዳሜዎች ለተቋሙ ባለአክሲዮኖች ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል፡፡

፬/ "የተሻሻለውን የመመሥረቻ ጽሁፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ማስመዝገብ ወይም ፈቃድ ያገኘበትን ስም መለወጥ፤"

፰/ ከአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ፳፮፣ ፳፯፣ ፳፰፣ ፳፱፣ ፴፣ ፴፩ እና ፴፪ ተጨምረው ከአንቀጽ ፳፮ እስከ ፴ ያሉት አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፴፫ እስከ ፴፯ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

**፳፮/ የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብት ጥበቃ**

"የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት እና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል መመሪያ ብሔራዊ ባንክ ሊያወጣ ይችላል፡፡"

**፳፯/ የብድር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት**

"ብሔራዊ ባንክ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትን ጨምሮ በፋይናንስ ተቋማት መካከል የሚደረግ የብድር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ስለሚደራጅበት፣ ስለአሰራሩና የወጪ መጋራትን በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡"

**፳፰/ የማስታወቂያ ይዘትን ስለመቆጣጠር**

"ማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በማንኛውም ጊዜ በብሔራዊ ባንክ እምነት ሀሰተኛ፣ አሳሳች፣ አደናጋሪ ወይም የሌላውን ጥቅም የሚጎዳ የተከፈለበት የሬድዮ ወይም የቴሌቪዥን ማስታወቂያ፣ ፖስተር፣ ቢልቦርድ፣ በራሪ ወረቀት ወይም ሌላ ሰነድ እና የተከፈለበት የጋዜጣና የመጽሄት ማስታወቂያ አውጥቶ ቢገኝ

1/ "The auditor of any microfinance institution shall submit to the National Bank a complete audit report, including audit findings and recommendations and a management letter, within the time limit set in the National Bank Directive. In addition, the external auditor of a microfinance institution shall report its audit findings and conclusions to the shareholders of the institution. "

7/ Sub Article (4) of Article 17 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (4);

4/ "register its amended memorandum of association and articles of association or alter the name under which it is licensed;"

8/ The following new articles 26, 27, 28, 29, 30, 31 and 32 are added after Article 25 of the Proclamation, and the existing articles 26 to 30 are renumbered as Article 33 to 37, respectively:

**26. Financial Consumer Protection**

"The National Bank may issue directive for protecting the right and interest of financial consumers."

**27. Credit-Information-Sharing System**

The National Bank may issue directive for the establishment, operation, and cost apportionment of credit-information-sharing system among financial institutions including microfinance institutions.

**28. Regulation of Advertisement**

"The National Bank may at any time direct a microfinance institution to withdraw, amend, or refrain from issuing a paid radio or television announcement, a poster, billboard, brochure, circular or other document, and a paid advertisement in regularly published newspaper or magazine that it considers to be false, misleading, deceptive, or offensive."

ተቋሙ ማስታወቂያውን እንዲያቋርጥ፣ እንዲያሻሽል ወይም ከማስተዋወቅ እንዲቆጠብ ብሔራዊ ባንክ ሊያዘው ይችላል፡፡"

፳፱/ **<u>ዋናና ወሳኝ ሥራን በውጭ አካላት ስለማሰራት</u>**

"አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወሳኝ ሥራቸውን በውጭ አካላት ስለሚያሰሩ በት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ዋናና ወሳኝ ሥራ" ማለት ቁጠባ መሰብሰብን፣ ብድር መስጠትን፣ የሀገር ውስጥ ሀዋላን፣ የአነስተኛ የመድን ሥራ እና ብሔራዊ ባንክ የሚወስነውን ሌሎች ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡"

፴/ **<u>በዲጅታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት</u>**

"በዲጅታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት ስለሚሰጥበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ይወስናል፡፡"

፴፩/ **<u>ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አገልግሎት ስለመስጠት</u>**

፩) በአዋጁ የተጠቀሱ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ብሔራዊ ባንክ ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት ለሚቋቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ፈቃድ ስለሚሰጥበትና ቁጥጥር ስለሚያካሄድ በት ሁኔታ ተጨማሪ ግዴታዎች ለመደንገግ መመሪያ ያወጣል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ "ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ የሚሠራ ተቋም" ማለት ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ብቻ እንዲሠራ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ብሔራዊ ባንክ ከመደበኛው የአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ጋር የወለድ ነፃ ተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራዎችን ለመቆጣጠር መመሪያ ያወጣል፡፡

**29. <u>Outsourcing of Critical and Important Functions</u>**

"Minimum conditions for outsourcing of critical and important functions shall be determined by the directive to be issued by the National Bank. For the purpose of this Article, "critical and important functions" of a microfinance institution include: functions related to deposits, loans, local money transfer, micro insurance and any other function as may be determined by the National Bank. "

**30. <u>Digital Financial Services</u>**

"Minimum conditions to provide digital financial services shall be determined by the National Bank directive."

**31. <u>Interest free microfinance service</u>**

1) "Without prejudice to the requirements specified under the provisions of the Proclamation, the National Bank shall issue directive to prescribe additional conditions of licensing, supervision and requirements to establish Interest Free Microfinance Institution. For the purpose of this Sub-Article, "Interest Free Microfinance institution" means a microfinance institution licensed by the National Bank to undertake only interest free microfinance business.

2) Without prejudice to Sub Article (1) of this Article, the National Bank may issue directive to regulate microfinance businesses related to interest-free deposit mobilization and fund utilization within a conventional microfinance service."

**፴፪/ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በአነስተኛ የፋይናንስ ዘርፍ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ**

፩/ "በአዋጁ አንቀጽ ፳፭ የተደነገገው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም ሙሉ በሙሉ የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለቤትነት ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያንና በኢትዮ ጵያውያን የጋራ ባለቤትነት የተቋቋሙ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የአክስዮን ባለቤት መሆን ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ማቋቋም ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው አግባብ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ቀጥታ የአንድ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም ባለአክስዮን ሲሆን ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የአክስዮን ባለቤት የሆነበት ሌላ ድርጅት የአንድ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ባለአክስዮን ሲሆን የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም እሱ ባለአክስዮን የሆነበት እና በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋሙ ባለአክሲዮን የሆነ ድርጅት በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋሙ የሚኖረው የአክስዮን ድርሻ ዋጋ በሙሉ ተቀባይነት ባለው የውጭ ምንዛሪ ብቻ የሚከፈል ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ግዴታ ቢኖርም:-

ሀ) ከአክስዮን ባለቤትነት የሚያገኘው የትርፍ ድርሻ፣

ለ) የአክስዮን ድርሻውን ለሌላ ሰው ሲያዛውር፣

ሐ) ባለአክስዮን የሆነበት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሲሸጥ ወይም ፈርሶ ሂሳቡ ሲሰራ፣ ወይም

መ) ሌሎች ከአክሲዮን ባለቤትነት ጋር በተያያዘ፣

የውጭ ሀገር ዜግነት ላለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም እሱ ባለአክሲዮን ለሆነበት ድርጅት እና በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ አክሲዮን ላለው

**32. Manner of Participation of Foreign Nationals of Ethiopian Origin in a Microfinance Business:**

1/ "Without Prejudice to Article 25 of thi Proclamation foreign nationals of Ethiopian origin or organizations owned fully by foreign nationals of Ethiopian origin, or jointly by foreign nationals of Ethiopian origin and Ethiopian nationals may be allowed to acquire the shares of an Ethiopian micro-financing institution or establish a micro-financing institution.

2/ If a foreign national of Ethiopian origin holds a share directly in a microfinance institution or indirectly by holding a share in another organization that holds a share in a microfinance institution, in accordance with the provisions of Sub Article (1) of this article, a foreign national of Ethiopian origin or the organization in which he is shareholder, shall pay the values of the shares in a microfinance institution only in an acceptable foreign currency.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this article, all types of payments due to a foreign national of Ethiopian origin resulting from:

a) dividends earned from a share in a microfinance institution;

b) transfer of shares in a microfinance institution;

c) sales or liquidation of a microfinance institution; or

d) any other matters related to shareholding in a microfinance institution;

shall be paid in local currency, i.e., Birr, meanwhile, he shall not be allowed to repatriate any asset or interest obtained in this manner.

የሚከፈሉ ማናቸውም ዓይነት ክፍያዎች በሙሉ በብር የሚከፈለው ይሆናል፣ እንዲሁም በዚህ አግባብ የሚያገኘውን ሀብት ወይም ጥቅም ወደ ውጭ ሀገር ማዛወር አይፈቀድለትም፡፡

፬/ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአነስተኛ የፋይናንስ ዘርፍ መዋዕለ ንዋያቸውን በሥራ ላይ ስለሚያውሉበት ተጨማሪ ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡"

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊድል ተራ (ሀ) እና አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንዲሁም አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሐ) ተሰርዘዋል፡፡

፲/ በአዋጁ በተለያዩ ቦታዎች "ተቆጣጣሪ" ወይም "የቁጥጥር ሥራ" የሚለው እንደ ቅደም ተከተላቸው "መርማሪ" ወይም "የምርመራ ሥራ" በሚል ተተክቷል፡፡

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

4/ The National Bank may issue directive related to additional conditions for investment in a microfinance institution by foreign nationals of Ethiopian origin. "

9/ Paragraph (a) of Sub Article (3) of Article 12 and Sub Article (1) of Article 13 as well as paragraph (c) of Sub Article( 2) of Article 14 of the proclamation are deleted.

10/ "Inspector" or "Inspection" mentioned in different parts of the proclamation is replaced by "Examiner" or "Examination" , respectively.

## 3. Effective Date

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 9th day of Junuary 2020.**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## ማረሚያ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፲፪

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፮/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፹፰ (፬)“ሠራተኛዋ ከመውለዷ በፊት የወሰደችው የ፴ የሥራ ቀናት የቅድመ፣ ወሊድ ፈቃድ ሲያልቅ ካልወለደች እስከምትወልድበት ቀን ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት እረፍት ልታገኝ ትችላለች፡፡ የ፴ የሥራ ቀናት የቅድመ-ወሊድ ፈቃዷ ሳያልቅ ከወለደች ፺ የሥራ ቀናት የድህረ ወሊድ ፈቃዷ ይጀምራል፡፡ የተባለው “ሠራተኛዋ ከመውለዷ በፊት የወሰደችው የ፴ ተካታታይ ቀናት የቅድመ፣ ወሊድ ፈቃድ ሲያልቅ ካልወለደች እስከ ምትወልድበት ቀን ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀ (፪) መሠረት እረፍት ልታገኝ ትችላለች፡፡ የ፴ ተከታታይ ቀናት የቅድመ-ወሊድ ፈቃዷ ሳያልቅ ከወለደች ፺ ተከታታይ ቀናት የድህረ-ወሊድ ፈቃዷ ይጀምራል፡፡”ተብሎ ይነበብ።

## Corrigendum No.15/2020

Article 88(4) of Labour Proclamation No. 1156/2019 which read as “Where a pregnant worker does not deliver within the 30 working days of her pre-natal leave, she is entitled to an additional leave until her confinement in accordance with Sub-Article (2) of this Article. However, if birth takes place before the expiry of the pre-natal leave, the 90 working days of post-natal leave shall commence.” is hereby corrected and shall be read as “Where a pregnant worker does not deliver within the 30 consecutive days of her pre-natal leave, she is entitled to an additional leave until her confinement in accordance with Sub-Article (2) of this Article. However, if birth takes place before the expiry of the pre-natal leave, the 90 consecutive days of post-natal leave shall commence.”